
# መረጃ፤ መፋታት ወይም መለያየት ለሚፈልጉ

## በትዳር ውስጥ ላሉ
## ተመዝግበው አብረው ለሚኖሩ የተመሳሳይ ጾታ አጋሮች
## ሳይጋቡ አብረው ለሚኖሩ ፍቅረኞች

### ባለትዳር ነኝ/የምኖረው በተመዘገበ አጋርነት ነው እና መለያየት እፈልጋለሁ።በመቀጠል ምን ማድረግ አለብኝ?

የጋብቻ ጥበቃ ሂደትን ከሚመለከተው የዲስትሪክት ፍርድ ቤት የጋብቻ ጥበቃ ሂደቶችን ማስጀመር ይችላሉ። የጋብቻ ጥበቃ ሂደት ማስጀመሪያ ቅጽ ለመክፈት ይህን ማስፈንጠሪያ ይጫኑ። ለመለያየት ወይም ለመፋታት የሚሞላውን ቅጽ በመሙላት የህግ ሂደቱን እራስዎ ወይንም ህጋዊ ውክልና በመስጠት የህግ ጠበቃዎ መጀመር ይችላል/ትችላለች። በመጀመሪያው ከህግ አማካሪዎች ጋር በሚኖርዎት ቀጠሮ ላይ የሚከተሉትን ሰነዶች ይዘው ቢሄዱ መልካም ነው:

- ገንዘብን በተመለከተ አሁን ያሉበትን የወጪና የገቢ ሁኔታ የሚያሳዩ ሰነዶችን፣ [የመጨረሻዎቹ ሁለት የግብር ተመላሾች እና የግብር ደረሰኞች፣ ከ 3 እስከ 6 ወራት የደሞዝ ወረቀቶች፣ ለመደበኛ ክፍያዎች ደረሰኞች ወጪዎች፣ ወጪና ገቢን የሚያሳይ የባንክ ሰነድ ከ3 እስከ 6 ወራት ውስጥ ያለውን]
- የጋብቻ ታሪካችሁን የሚያሳዩ ማስታወሻዎች ሰነዶች [አስፈላጊ የሆኑ ክስተቶችን የሚያሳዩ፣ ፋይሎች ለምሳሌ ባል ወይም ሚስት ያደረሡትን በደል የሚያሳይ የህክምና ማስረጃ ወይም የወንጀል ሂደቶችን እንዲሁም የጥቃት መከላከያ እርምጃዎችን የሚያሳዩ ሰነዶች]



### የጋብቻ ጥበቃ ሂደት ምን ያህል ያስከፍላል እና ለጠበቃ የሚከፍለው ማን ነው?

ገቢዎ አነስተኛ ከሆነና የገንዘብ እጥረት ካለብዎ እርስዎ ወይም የህግ ተወካይዎ ለነጻ ክርክር እና ህጋዊ ውክልና ማመልከቻ ማስገባት ይችላሉ። ነጻ የህግ ጠበቃና የህግ አገልግሎ ለማግኘት የሚረዳ መረጃ ሊንክ።
ማመልከቻው ተቀባይነት ካገኘ የፍርድ ቤቱን እና የጠበቃዎ ወጪዎች ለጊዜው በመንግስት ይሸፈናሉ። ለወደፊቱ የተሻለ ገቢ ኖሮዎት ከበቂ በላይ ገንዘብ ማግኘት ከጀመሩ፣ ፍርድ ቤቱ የፍርድ ቤቱን እና የውክልና ወጪዎችን በ10 ዓመታት ውስጥ እንዲከፍሉ ሊጠይቅ ይችላል። ጋብቻ ጥበቃ ማመልከቻውን ከሰረዙ፣ እስከዚያ ድረስ ያወጡትን የህግ እና የፍርድ ቤት ወጪዎች እራስዎ መሸፈን ሊኖርብዎት ይችላል። በነጻ የፍትህ አስተዳደር ላይ መረጃ ሊንክ። የውክልና ወጪዎችን እራስዎ መሸፈን ከቻሉ፣ ስለ ጋብቻ ጥበቃ ሂደት ክፍያው ምን ያህል እንደሆነ መረጃ ከህጋዊ ምክር አገልግሎት ከሚሰጥበት ቦታ ወይም ከጠበቃዎ ማግኘት ይችላሉ።

### የጋብቻ ጉዳይና ጥበቃ ፍርድ ቤት የሚያነሳቸው ነጥቦች የትኞቹ ናቸው?

የጋብቻ ጥበቃ ፍርድቤቱ በሚከተሉት ነጥቦች ላይ ውሳኔ ያሳልፋል።

- የመኖሪያቤት ውስጥ ማን እንደሚቆይ፣
- ልጆቹን የመንከባከብ ሃላፊነት የማን እንደሆነ፣
- መተዳደርያን በተመለከተ፣
- ንብረት ክፍፍልን በተመለከተ

### ባለቤቴ መለያየት መፈለጌን ሲሰማ ነገሮች በጣም እንዳይባባሱ እፈራለሁ፤

ባለቤትዎ በእርሶና በልጆቻቹ ላይ በደል ያደርሳል? በእርሶና በልጆቻቹ ላይ ጥቃት ይፈጽማል? ወይም ጥቃት አደርሳለው እያለ ያስፈራራችዋል? ፖሊስ በጉዳዩ ጣልቃ በመግባት ጥበቃ ሊያደርግላችሁና አስፈላጊውን የመከላከል እርምጃ ሊወስድ ይችላል:: (ከጥቃት የመከላከል ህግ) አጋርዎን ከምትኖሩበት ቤት ወይም አፓርታማ እንዲባረሩ ማድረግና እርሶዎና ልጆችዎ የሚገኙበት አካባቢ እንዳይመጡ ማድረግ እንዲሁም እርሶንም ሆነ ልጆችዎን እንዳያገኙ ለ14 ቀን ማሳገድ ይችላሉ። አስፈላጊ ከሆነም በ 8 ቀናት ውስጥ እነዚህን የመከላከያ እርምጃዎች አንድ ጊዜ ለ 3 ወራት ለማራዘም ይችላሉ። የተጎጂዎች ምክር ማእከላት (Opferberatungstellen) በነጻ እና ሚስጥሮን በታማኝነት በመያዝ ድጋፍ በማድረግ የምክር አገልግሎት በመስጠት ይተባበርዎታል። እነዚህ 3 ወራት አብዛኛውን ጊዜ ህጋዊ መለያየት ለማድረግ በቂ ናቸው። የመከላከል እርምጃ ገደቡ ሲያበቃ የኑሮ አጋርዎ እንድገና ዛቻና ማስፈራራት እንዳይጀምሩ ከፈሩ አስፈላጊ ጥበቃ እንዲደረግሎዎና ባለቤትዎ እርሶ ባሉበት አካባቢ እንዳይደርስና እገዳ እንዲደረግበት አካባቢዎ ባለው የአውራጃ ፍርድቤት ማመልከቻ ማስገባት ይችላሉ (የፍትሐ ብሔር ህግ 28 ZGBb) ። አስፈላጊሆኖ ካገኙት ለመለያየት ሲያመለክቱ የዕገዳ ጥያቄውንም አብረው ማመልከት ይችላሉ። የግል ጥበቃ ብሄራዊ ፍርድ ቤት ይህንኑ ማመልከቻ በተመሳሳይ ጊዜ ለጋብቻ ጥበቃ ፍርድቤት ማቅረብ ይችላሉ። ይሄን በተመለከተ ያለውን አማራጭ ከጠበቃ ጋር ወይም የህግ ምክር አገልግሎት ማእከል በመሄድ ይጠይቁ። ባለቤትዎ ወደ እርስዎ እንዳይቀርብ የተሰጠውን እገዳ ተላልፎ ሊያጠቃኝ ይችላል የሚል ፍርሃት ካለዎት በትዳር ጓደኞቻቸው የተጠቁን ሴቶች ደህንነት የሚጠብቅና አስተማማኝ ማቆያ ቦታ ያለውን የሴቶች ቤት በመባል ወደሚታወቀው ተቋም ቢሄዱ ሊረዱዎ ዝግጁዎች ናቸው።

### መለያየቱ በጣም በፍጥነት መደረግ ካለበት?

በጋብቻ ጥበቃ ሂደት ፍርድቤት በጣም አስቸኳዋይና ጊዜያዊ እርምጃዎች እንዲወሰዱ ማመልከት ይችላሉ። የሚረዳዎት ደሞ የደረስቦትን ጥቃትና የጉዳዩን አጣዳፊነት በማስረጃ ማቅረብ ነው። በተጨማሪም መገለጽ ያለበት ሊጠገን በማይችል ጉዳት ምክንያት የተጠየቀው ደንብ በአስቸኳዋይ ካልተደረገ የሁለቱም ተከራካሪዎች ሃሳብ ሳይሰማ ይተገበራል። ፍርድ ቤቱ ልክ እንደ የጋብቻ ውል አፍራሽ ፍርድቤት በጊዜያዊነት – ነገር ግን በፍጥነት – ተመሳሳይ ነጥቦችን ቢያንስ በከፊል ይመለከታል:: በጊዜያዊነት ለሚወሰዱ እርምጃዎች የሚያስፈልጉ መስፈርቶች በጣም ከፍተኛ ናቸው ቀጥሎ የሚጠብቅዎትን ነገር ለማወቅ የህግ አማካሪዎችን ያናግሩ።

### ቤቱ ውስጥ ሊቆይ የሚችለው ማን ነው?

በህጉ መሰረት ቤቱ ውስጥ ሊቆይ የሚገባው ፣ ልጆቹን እንዲንከባከብ የተወሰነለት ከወላጆቹ አንዱ አካል ነው። በትዳር በኖራችሁበት ቤት ውስጥ መቆየት ከፈለጉ ፣ የሚከተሉትን ነገሮች በማመልከቻ መጠየቅ ይችላሉ ፣

- የኑሮ አጋርዎ የሚለቀቅበት ቀን (ከጥቂት ቀናት እስከ ሁለት ወራት) ሊሆን ይችላል። የኑሮ አጋርዎ የመኖሪያ ቤታችሁን በፈቃደኝነት ለመልቀቅ እንደማይፈልግ ማስረጃ ካለዎት ከከተማው ከንቲባ ጽ/ቤት ለማባረር የሚያስችሎትን ፍቃድ ይጠይቁ።
- ያለእርስዎ እውቅና የኑሮ አጋርዎ ቤት ውስጥ እንዳይገባ፣ ሁሉንም የቤቱን ቁልፎች መመለስ አለበት። ሆኖም የኑሮ አጋርዎ ሁሉንም ቁልፎች አልመለሰም የሚል ጥርጣሬ ካለዎትና ፍርሃት የሚሰማዎት ከሆነ ፣ የቤቱን የቁልፍ ጋንና ቁልፎቹን ማስቀየር ይችላሉ።

### ልጆች መኖር ያለባቸው ከማን ጋር ነው?

ልጆች መኖር ያለባቸው እስካሁን ልጆቹን በይበልጥ ይንከባከብ ከነበረው ወላጅና ወደፊትም በዚሁ ሁኔታ ሊቀጥል ከሚችለው ወላጅ ጋር ነው።

ፍርድቤቱ ለልጆቹ እድገት የተሻለውን ወላጅ ለመወሰን የራሱን ምርመራ ያደርጋል። ባጠቃላይ ወንድማማቾችና እህትማማቾች በፍጹም መለያየት የለባቸውም።

በውሳኔው ሂደት ላይ እድሜያቸው በአማካይ 6 አመትና ከዚያም በላይ የሆናቸው ልጆችም ሃሳብ ይካተታል።

## ሌላው ወላጅ ምን ያህል ጊዜ ልጆቹን ይንከባከባል?

እንደ ደንቡ ሁለቱም ወላጆች ከተለያዩ በኋላም ቢሆን ልጆችቻቸውን በጋራ የመጠበቅ ፣ የማሳደግ እና በተለያየ ጊዜ የመንከባከብ ኃላፊነት አለባቸው። ልጆቹን የምትረካካቡበት ሰአት በጥብቅ መከበርና ቋሚ መሆን አለበት። እንዲሁም በእረፍት ጊዜ፣ እንደ ፋሲካ፣ ጾራቅሊጦስ እንዲሁም ገና እና ለመሳሰሉት በዓላት ላይ ልጆቹ ከማን ጋር እንደሚያሳልፉ ደንብ ማውጣታችሁን እርግጠኛ ሁኑ።

ባለቤትዎ ልጆቹን የሚመታቸውና የሚያስፈራራቸው ከሆነ፣ ልጆቹ በሄዱ ቁጥር ሁከትና ችግር የሚፈጥር ከሆነና እየባሰበት ከሄደ ልጆቹ እሱ ጋር በሚሄዱበት ጊዜ አብሮቸው የሚቆይ ሰው እንዲመደብላቸውና በመሃከላችሁ የጉብኝት ሰአቱን የሚያስተካክል ሰው እንዲመደብላቹ የሚመለከተውን ክፍል መጠይቅ ይችላሉ። ልጆችን የመንከባከብ ሃላፊነት የሚነሳው ግን ልጆቹ ለትልቅ አደጋ ከተጋለጡ እና አብዛኛውን ጊዜ ለተወሰነ ጊዜ ብቻ ከሆነ ነው።

ከባለቤትዎ ጋር የልጆቹን ሃላፊነት በመውሰድና በመንከባከብ ጉዳይ ካልተስማማቹ ፍርድቤቱ የራሱን ውሳኔ ይወስናል። ፍርድ ቤቱ ራሱ ለዚህ ጉዳይ ሲባል የልጆች ተወካይ ሊሾም ይችላል ወይም እርስዎ እራስዎ ለፍርድ ቤቱ የልጆች ጠበቃ እንዲያደርግሎት ማመልከት ይችላሉ። ክፍያው በወላጆች መሸፍን አለበት ግን ወላጆች አቅም ከሌላቸውና የህግ ድጋፍ የማግኘት መብት ካላቸው መንግስት ወጭያቸውን ሊሸፍን ይችላል።

## በምን እንተዳደር?

ፍርድ ቤቱ ለመተዳደሪያ የሚሆኖትን ገንዘብ እስኪወስንልዎት ድረስ ሳምንታት ወይንም ወራት ሊወስድ ይችላል በመሆኑም የፍቺውን ጉዳይ ለያዘው የጋብቻ ጥበቃና የፍቺ ፍርድቤት ማመልከቻዎን ካስገቡ በኋላ በቂ ገንዘብ ከሌለዎት ለጥንቃቄ ሲባል ለመንግስት ድጎማ ቢሮ ጥያቄዎን ማቅረብ አለብዎት። ከመንግስት የገንዘብ እርዳታ የማግኘት መብት አለዎት። ከባለቤትዎ ጋር የጋራ የባንክ ደብተር ወይም ክሬዲት ካርድ ካላቹ ፡

- በተጨማሪም የባንክ ደብተሩ ወይም ክሬዲት ካርዱ በባለቤትዎ ስም ከሆነ እንዲሁም እጅዎ ላይ በቂ ገንዘብ ከሌለዎት ለ 3 ወር ያህል የሚበቃዎትን ገንዘብ በአስቸኳይ ያውጡ።
- የባንክ ደብተሩ ወይም ክሬዲት ካርዱ በእርሶ ስም ከሆነ ደግሞ ባለቤትዎ በካርዱ እንዳይጠቀም በአሰቸኳይ ማዘጋት አለብዎት።

ጉዳዩን የሚያየው በጋብቻ ጥበቃ ፍርድቤት የሁለቱም ቤተሰቦች ፍላጎት ተሰልቶ ከገቢያቸው ላይ ተቀናሽ ይደረጋል። ፍላጎቶች ከተሸፈኑ በኋላ ትርፍ ካለ፣ ይህ በዋነኝነት የልጆቹን ፍላጎቶች ለመሸፈን እና በሁለተኛ ደረጃ ለኑሮ አጋርዎ ያለውን ጉድለት ለመሸፈን ያገለግላል። ወጪዎችዎ በሚያገኙት ገቢ እና በጥገና ክፍያ መሸፈን ካልቻሉ፣ ከማህበራዊ ቢሮ(ሶሻል ቢሮ) እርዳታ የማግኘት መብት አለዎት። ከተለያዩ፣ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ተቀጥረው ባይሠሩም እንኳ፣ ለሥራ አጥ የሚከፍለውን ክፍያ የማግኘት መብት ሊኖርዎት ይችላል።
በጋብቻ ጥበቃ ፍርድ ውስጥ የሚወሰነው የልጅ ማሳደጊያ ክፍያዎች በመንግስት ሊሸፈን ይችላል። የቅድሚያ ክፍያው በከፍተኛው የልጁ የ AHV/IV ጡረታ መጠን ላይ የተመሰረተ ነው (በ2023 ይህ CHF 980 ነበር)።
ለትዳር አጋሮች የቅድሚያ ክፍያ የለም። የሚኖሩበት ቀበሌ(ገማይንዴ) የኑሮ አጋርዎ መተዳደሪያችሁን በትክክል ካልከፈሉ የሚከፍለውን አካል ቀበሌው በእዳ ወደ ሚጠየቁበት ቢሮ (Betreibung) ያስተላልፋቸዋል።

## መለያየቱ በመኖሪያ ፈቃዴ ላይ የሚያመጣው ተጽእኖ አለ ወይ?

አብዛኛውን ጊዜ ስዊዘርላንድ ውስጥ በጋብቻ ወረቀት ያገኘ ሰው ስዊዘርላንድ ውስጥ የመኖር መብቱ ከትዳር አጋሩ ጋር የተያያዘ ነው። (ለምሳሌ በቤተሰብ ውህደት የሚገኝ ቤ(B) ወረቀት) በእርግጥ ስዊዘርላንድ ውስጥ ለመኖር የተሻለ መመዘኛና አማራጭ ባላቸው የአውሮፓ ህብረት አገራት ዜጎች እና የሶስተኛ አለም አገራት መሃከል ህጉ ልዩነት አለው። የአውሮፓ ዜግነት ለሌላቸው ሰዎች ከትዳራቸው ሲለያዩ ፈቃዳቸውን ለማራዘም የሚችሉበት መንገድ አለ፡ ይኸውም ከሶስት አመት በላይ ስዊዘርላንድ ውስጥ በትዳር የቆዩና አስተማማኝ በሆነ መልኩ ባህሉን፣ ቋንቋውንና ወዘተ... የለመዱ ከሆኑ(ኢንተግሬት ያረጉ)ከሆኑ፣ እንዲሁም አሳማኝ የሆነ የግል ምክንያት በማቅረብ ፈቃዳቸውን ማሳደስ ይችላሉ። በተለይም በትዳራቸው ላይ የደረሰባቸው በደል ካለ ወይንም ወደ አገራቸው መመለሳቸው አደጋ ላይ የሚጥላቸው ከሆነ ነው።

በተለይ ደግሞ በትዳሮ ተበድለው ከሆነና ጉዳት ደርሶብዎት ከሆነ በተቻለዎት መጠን የሀኪም ማስረጃዎችን ፣ ከሴቶች ጥበቃ ቤት፣ ወይም ከምክር አገልግሎት ተቋማት፣ በደልዎን በሚመለከት የተሰጠዎት ወረቀት ካለ፣ እንዲሁም ከፖሊስ የተሰጠዎት ማንኛውም አይነት ማስረጃ ካለ በጥንቃቄ ማስቀመጥ አለብዎት። የመኖሪያ ፈቃድዎን እንዳይነጠቁ በመስጋት ብቻ በደል እየደረሰብዎት ቤት ውስጥ መቆየት የለብዎትም። ይህን በተመለከተ በነጻና በታማኝነት የምክር አገልግሎት እንሰጥዎታለን።

## የጋብቻ ጥበቃ የፍቺ ውል ችሎት የሚደረገው ስምምነት ምንድነው?

የጋብቻ ጥበቃ ሂደት ችሎት ያለውን ሂደት በተመለከተ ከምክር አገልግሎት ተቋም ከጠበቃ ወይም ከፍርድ ቤት መረጃ ማግኘት ይችላሉ። ወደ ፍርድ ቤቱ የሚሄዱት ያለጠበቃ ከሆነ

- እርግጠኛ ያልሆኑበትን ስምምነት ሁሉ እንዳይፈርሙ ።
- የሚፈርሙ ከሆነ ደግሞ በ10 ቀን ውስጥ ውሳኔዎን መቀልበስ መቻልዎትን ያረጋግጡ። ከዛም ውሳኔውን ለህግ አማካሪዎች ያሳዩና ስምምነቱ እርስዎን የሚጠቅም ካልሆነ በተባለው10 ቀን ውስጥ ሃሳብዎን መቀየርዎን ለፍርድቤቱ ያሳውቁ።

ልጆችን ወደዚህ ፍርድ ቤት ይዞ መምጣት ክልክል ነው። ስለሆነም ጉዳይዎን ተረጋግተው እንዲጨርሱ ልጆችዎን ለግማሽ ቀን የሚይዝልዎት ሰው ቢያዘጋጁ መልካም ነው። የጀርመንኛ ቋንቋ በደንብ የማይናገሩና የማይረዱ ከሆነ ቀደም ብለው አስተርጓሚ እንዲመደብልዎ ይጠይቁ።

## በፍርድቤቱ ውሳኔ ካልተስማማሁ ምን ማድረግ እችላለሁ?

በፍርድቤቱ ውሳኔ ካልተስማሙ በ10 ቀን ውስጥ ይህ ውሳኔ የተወሰነበትን ምክንያት እንዲሰጥዎ ይጠይቁ። የተወሰነበትን ምክንያት ከተቀበሉ በኋላ በተሰጥዎ ቀናት ውስጥ ይግባኝ መጠየቅ ይችላሉ። (በውሳኔው ወረቀት መጨረሻ ላይ ያሉትን የህግ መተግበሪያዎች በጥንቃቄ ይመልከቱ።) በተሰጠዎት ቀን ውስጥ ምንም አይነት ተቃውሞ ካላቀረቡ ውሳኔው ይጸናል። ውሳኔው እንዲቀየር መጠየቅ የሚችሉት ከፍርዱ በኋላ ሁኔታው በጣም ጉልህና ቋሚ በሆነ ሁኔታ ከተቀየረ ብቻ ነው።

## ከእንደገና አብረን መሆን ብንፈልግስ?

ከባለቤትዎ ጋር ተመልሰው አብረው መኖር ከፈለጉ ውሳኔው ከ3–5 ባሉት ሳምንታት ውስጥ በራሱ ይሻራል።
ከእንደገና ከተለያያቹ ደግሞ የጋብቻ ጥበቃ ሂደት እንደገና እንደአዲስ ይጀመራል።

## በአስቸኳይ ወድያውኑ መፋታት አይሻለኝም?

ሁለታችሁም ለመፋታት ከተስማማችሁና ለወረዳው ፍርድቤት ካረጋገጣችሁ ፍቺውን በማንኛውም ጊዜ ማድረግ ይቻላል። ነገር ግን ከልምድ እንደሚታየው ሰዎች ለመፋታት ፍርድቤት ከጠየቁ በኋላ ሃሳባቸውን ይቀይራሉ፣ በመሆኑም ለመተዳደሪያ

የሚከፈለውን ክፍያ፣ የልጆቹን ሃላፊነትና የመኖሪያ ቤቱን በተመለከተ ለመወሰን ወደ የጋብቻ ጥበቃና ፍርድቤት መሄዱ ሂደቱን ያቀለዋል። ከባለትዳሮቹ አንደኛው ቶሎ ለመፋታት የማይስማማ ከሆነ በህጉ መሰረት ሁለት አመት መጠበቅ አለባቸው።

ነገር ግን አብሮ የመኖራቸው ተስፋ ያከተመለት ከሆነና አንዱ ወገን የፍቺ ክስ ሊያቀርብ ይችላል ይሁን እንጂ ሂደቱ ብዙ እንቅፋት ያለበትና ክርክር የበዛበት ከሆነ ውስብስብ ስለሚሆን ከ 2 አመት በላይ የፍርድ ቤት ሂደቱ በጣም ረጅም ጊዜ ሊወስድ ይችላል። የጋብቻ ጥበቃ ና የፍቺ ውል ግን በተሻለ ፍጥነትና ግልጽ ያለ ነገር ያመጣል። ለማንኛውም ከምክር አገልግሎት ተቋም፣ ከህግ አማካሪ ወይም ከፍርድ ቤት ምክርን ይጠይቁ።

## የማልፈልገውን ጋብቻ እንድፈጽም ከተገደድኩኝ ምን ማድረግ እችላለሁ?

ስዊዘርላንድ ውስጥ የሚኖር ሰው ሁሉ ነጻ የሆነ የትዳር ምርጫ የማድረግ መብት አለው። የስዊዘርላንድ ህግ በሃገር ውስጥም ሆነ ከሃገር ውጪ የሚደረገውን የግዴታ ጋብቻን የሚቃወም ነው። አስፈላጊ ከሆነ ይሄንን ድረገጽ መመልከት ይችላሉ www.zwangsheirat.ch ወይም የተጎጂዎችን ምክር ማእከል ያነጋግሩ። እንዲሁም በተለያዩ ቋንቋዎች ነፃ የምክር አገልግሎትና እና ድጋፍ ያገኛሉ።

## ከተመሳሳይ ጾታ ጋር በፍቅር ግንኙነት ላይ የተደረገን ህጋዊ ስምምነት ለማፍረስ ምን ማድረግ አለብኝ?

ከጁላይ 1 ቀን 2022 በፊት አንድላይ ለመሆን የተመዘገቡ የተመሳሳይ ጾታ ጥንዶች መለያየት ከፈለጉ በአካባቢያቸው ፍርድ ቤት የመለያየት ሂደቱን ሊጀምሩ ይችላሉ። እርስዎ እና አጋርዎ በመለያየቱ ላይ መስማማት ካልቻላቹ፣ የተመዘገበ አጋርነት ሲፈርስ የተወሰነው የመለያያ ጊዜ 1 ዓመት ነው። እንደ የጋብቻ ጥበቃና የፍቺ ውል ሂደት በፍርድቤትም ነጥቦቹ የተደነገጉ ናቸው።
ከኑሮ አጋርዎ በደል ወይም ማስፈራራት የሚደርስብዎት ከሆነ ፖሊስ ባለው ተበዳዮችን የመከላከል ስልጣንና ሃላፊነት መሰረት ጉዳዩን እንዲከታተልና ጥበቃ እንዲያደርግልዎት መጠየቅ ይችላሉ።

## ከፍቅረኛዬ ጋር ትዳር ሳንመሰርት አንድ ላይ እንኖራለን አሁን ግን መለያየት እፈልጋለሁ (ኮንኩቢናት)

ከፍቅረኛ ጋር ሳይጋቡ መኖር ( ኮንኩቢናት) በህግ ላይ የተመሰረተ ትሥሥር አይደለም። ቢሆንም መለያየት በሚፈጠርበት ጊዜ የሚከተሉትን ነጥቦች ማወቅ ጠቃሚ ነው።

- የጋራ ልጆችን በተመለከተ፣ እነሱን የመንከባከብ ሃላፊነት የማነው የሚለውን ሂደት የሚታየው በ ህጻናትና ጎልማሶች ጥበቃ ባለስልጣን KESB ነው። ለበለጠ መረጃ የክልሉን የህግ አገልግሎት ማግኘት ይችላሉ።
- ለልጆች መተዳደሪያ በሚወሰነው ቀለብ መጠን ላይ ካልተስማሙ በሚኖሩበት ቦታ የሚገኘው የወረዳ ፍርድ ቤት ይህንን ይወስናል።
- በዋነኝነት ልጆቹን የሚንከባብከው አካል ህጋዊ ጋብቻ ከሌለው በሚለያዩበት ጊዜ የሚወሰንለት መተዳደሪያ አይኖርም። ፍርድ ቤቱ ቀለብ የመወሰን ሃላፊነት እንደወሰደ፣ የልጆቹን እንክብካቤ የመቆጣጠር ሃላፊነት ከKESB ወደ ፍርድ ቤት ይቀየራል።

በመኖሪያ ቤት ውስጥ የሚቆየው አካል መቆየት የሚችለው በእርሱ ፣ በአከራዩና በተለያየው ፍቅረኛው መሃከል በተደረገው የቤት ኪራይ ስምምነት ይወሰናል። ህጋዊ ጋብቻ ሳይፈጽሙ አብረው የኖሩ ሰዎች ሲለያዩ የሚኖረው ውጣ ውረድ አስቸጋሪ ስለሆነ የምክር አገልግሎት ተቋሞችን ማነጋገር ወይንም የህግ ጠበቃ ማናገሩ ይበጃል። የፍቅር አጋርዎ በእርስዎም ላይ ሆነ በልጆቹ ላይ በደል የሚፈጽም ከሆነ በህጉ መሰረት ጥበቃ እንዲደረግልዎት መጠየቅ ይችላሉ።
(ስለ ደህንነት በራሪ ወረቀት)

ምልክት የተደረገባቸው ጽሁፎች ወደ ድረገጾች እና ሰነዶች የሚወስዱ መስፈንጠርያዎች ናቸው። በዚህ ኪወ አር ኮድ ሊከፍትዋቸው ይችላሉ ።

## ጠቃሚ አድራሻዎች:

**የጋብቻ ጥበቃ ሂደቶች መግቢያ**
በሚኖሩበት ቦታ የሚገኘው የወረዳ ፍርድ ቤት
የጋብቻ ጥበቃ ሂደት ቅጽ

**የሕክምና እርዳታ እና የምስክር ወረቀቶች**
www.permanence.ch
ስልክ: 044 215 44 44

**የሕግ ባለሙያዎች / ጠበቆች ማህበር**
www.zav.ch
www.anwaltskollektiv.ch
www.djs-jds.ch

**ሳይጋቡ አብሮ መኖር እና ልጆች**
www.zh.ch
የወላጅ ሃላፊነት

**ጥበቃ**
የፖሊስ የድንገተኛ አደጋ ቁጥር 117
የሴቶች መጠለያ:
www.frauenhaeuser.ch

**ማስረጃ ማሰባሰብያ**
www.with-you.ch

**የተጎጂዎች ድጋፍ ለሴቶች**
www.bif-frauenberatung.ch
www.frauennottelefon.ch
www.frauenberatung.ch

**ለልጆች ድጋፍ**
www.kokon-zh.ch
www.okeywinterthur.ch
www.kinderanwaltschaft.ch



**BIF Beratungsstelle für Frauen**
gegen Gewalt in Ehe und Partnerschaft

Postfach, 8031 Zürich
Tel. 044 278 99 99
www.bif-frauenberatung.ch
info@bif.ch

PC 87-137016-4
IBAN: CH32 0900 0000 8713 7016 4

Opferhilfe Zürich

LGBTIQ+ FRIENDLY

* ለተሻለ ተነባቢነት ሲባል፣ ለትዳር አጋሮች የወንዶችን ጾታ ብቻ ነው የተጠቀምነው። ቢሆንም ሁሉንም የራሳቸው የፆታ ማንነት ያላቸው ሰዎች ያካትታል።

© 2025, ለአርታዒ, BIF